

የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት
Road Safety & Insurance Fund Service

የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክን ለመቆጣጠር የወጣውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 557/2016 መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ

በአሽከርካሪዎች የሚፈፀሙ ጥፋቶች፣ የጥፋቶቹ እርከን፣ ለጥፋቶቹ የሚመዘገብ ነጥብ እና የገንዘብ ቅጣት መጠን

2017 ዓ.ም

CamScanner

በአሸከርካሪዎች የሚፈጸሙ ጥፋቶች እና የጥፋቶቹ እርከንናለጥፋቶቹ የሚቆጠር የቅጣት ነጥብ እና የቅጣት መጠን ወይም የሚወሰድ እርምጃ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት
ደንብ ቁጥር 557/2016

2017 ዓ.ም

አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 557-/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ዓላማ

የዚህ ደንብ ዓላማ ዓለም አቀፍ የመንገድ ትራፊክን የሚመለከት የተጠቃለለ እና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ደረጃዎችንና ስልቶችን በማስቀመጥ በሀገራችን ያለውን የመንገድ ደህንነት ከፍ ወዳለ ደረጃ በማሳደግ በመንገድ ትራፊክ የሚደርሰውን አደጋ መቀነስ ነው::

የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ የኢትዮጵያን መንገዶች በሚገለገሉና በሚንቀሳቀሱ ሁሉም ተሽከርካሪዎች፣ አሽከርካሪዎች እና የመንገድ ተጠቃሚዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

SAMUEL GIRMA

1. በአሽከርካሪዎች የሚፈጸሙ ጥፋቶች እና የጥፋቶቹ እርከን

ሀ/ አንደኛ ደረጃ የጥፋት ዝርዝር

ነ. ተሽከርካሪ ያለአግባብ የጎተተ

2. የግጭት መከላከያ ቆብ (ሄልሜት) ሳያደርግ ወይም አድርጎ ሳያስር ብስክሌት የነዳ ወይም የብስክሌቱን መሪ በእጁ ሳይዝ የነዳ፤

3. በተሽከርካሪው ውስጥ የተሟላ የመጀመሪያ ዕርዳታ መስጫ ኪት እና የሚሰራ የድንገተኛ አሳት ማጥፊያ መሳሪያ ሳይኖረው የንግድ ተሽከርካሪ ያሽከረከረ፤

4. የሚበኑ ወይም የሚበተኑ ነገሮችን ያለአግባብ ጭኖ ያሽከረከረ፤

5. ጭነትን እያፈሰሰ ወይም እየጣለ ያሽከረከረ ወይም ያፈሰሰውን ወይም የጣለውን ጭነት ሳይጠርግ ወይም እንዲጠረግ ሳያደርግ ጉዞውን የቀጠለ አሽከርካሪ፤

6. በትራፊክ መብራት ላይ ወይም በመስቀለኛ መንገድ ላይ በልመና ለተሰማሩ ሰዎች ገንዘብ የሰጠ ወይም ግብይት ያደረገ፤

7. ሲጋራ እያጨሰ ያሽከረከረ፤

8. የአደጋ ጊዜ አገልግሎት ተሽከርካሪን የአደጋ አገልግሎት ስራ ላይ ሳይሆን አላግባብ የተፈቀደለትን የድምጽና የአደጋ ምልክት መብራት በመጠቀም ያሽከረከረ፤

9. ከ13 አመት በታች የሆነን ሕጻን ከአሽከርካሪው ጎን በሚገኘው የተሽከርካሪው ከፍል (ጋቢና) ውስጥ አስቀምጦ ያሽከረከረ፤

10. ለጉዳት ተጋላጭ ለሆኑ የመንገድ ተጠቃሚዎች ተገቢውን ድጋፍና ጥንቃቄ ሳያደርግ ያሽከረከረ አሽከርካሪ፤

ለ/ ሁለተኛ ደረጃ የጥፋት ዝርዝር

1. የተሟላ የጭነት ማቀፊያ /ስፓንዳ/ ሳይኖረው ጭነት ጭኖ ያሽከረከረ፤

2. የጥሩምባ ድምጽ ያለአግባብ ወይም በተከለከለ ቦታ ላይ የተጠቀመ ወይም ተገቢ ባልሆነ የማስጠንቀቂያ (የጥሩንባ) ድምጽ የተጠቀመ፤

3. በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ ያጠበ ወይም እንዲታጠብ ያደረገ፤

4. በአውቶቡስ ማቆሚያ ስፍራ ላይ፣ በእግረኛ መንገድ ላይ፣ በትራፊክ ምልክት ወይም መብራት አጠገብ፣ በተሽከርካሪ መግቢያ ወይም መውጫ በር ላይ፣ ሌላ ተሽከርካሪ ደርቦ፣ ወይም በመንገድ ምልክት አማካኝነት ማቆም በተከለከለበት ማናቸውም ስፍራ ላይ ተሽከርካሪ ያቆመ፤

5. የአሽከርካሪውን ዕይታ የሚከለክል መጋረጃ፣ ተለጣፊ ላስቲክ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን በተሽከርካሪው ላይ ያስቀመጠ ወይም የለጠፈ፤

6. ከተፈቀደው ፍጥነት በታች ያሽከረከረ ወይም የቀኙን ጠርዝ ሳይዝ በዝግታ ያሽከረከረ፤

7. ከመጠን በላይ ድምጽ እያሰማ ወይም በጅሮ ማዳመጫ እያዳመጠ ያሽከረከረ፤

8. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሮት ሳይዝ ያሽከረከረ ወይም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ሳይሳድስ ያሽከረከረ ፤

9. በሕግ በተፈቀደው ርቀት ምልክት ሳያሣይ የተጠመዘዘ፣ አቅጣጫ የቀየረ፣ ተሽከርካሪ የቀደመ ወይም ተሽከርካሪ ያቆመ፤

10. በመንገድ ላይ ያለን ውሀ በተሽከርካሪው አማካኝነት በእግረኛ ላይ እንዲረጭ ያደረገ፤

11. የትራፊክ ምልክት ወደ ቀኝ ብቻ መታጠፍ በሚፈቅድ መንገድ ላይ መንገድ የዘጋ፤

12. በተከለከለ ቦታ ላይ ወይም የመንገዱን ቀኝ ዳር ሳይዝ ተሳፋሪ ወይም ዕቃ የጫነ ወይም ያወረደ፤

13. በማብሪያ ጊዜ መብራት እያለው ሳያበራ ያሽከረከረ፤

14. በጠባብ መንገድ ላይ ወይም በመታጠፊያ መንገድ በ12 ሜትር ውስጥ ተሽከርካሪ ያቆመ፤

15. ለአግረኛ ወይም ተላላፊ ቅድሚያ ያልሰጠ ፤

16. ቅድሚያ መስጠት ላለበት ተሽከርካሪ ቅድሚያ ያልሰጠ፤

17. በትራፊክ ደሴት ላይ ያሽከረከረ ወይም የመንገድ አከፋፋይ ደሴትን / መስመርን/ በማቋረጥ ያሽከረከረ፤

18. ከተፈቀደለት ጊዜ በላይ የተበላሸ ተሽከርካሪን መንገድ ላይ ያቆመ ወይም አቁሞ የጠገነ፤

19. የሚታጠፍበትን አቅጣጫ ሳይዝ ወይም ደርቦ የታጠፈ፤

20. ሁለት መስመር ባለው መንገድ ላይ በቀኝ በኩል ተሽከርካሪ የቀደመ፤

21. ምልክት ሳያሳይ ተሽከርካሪ ያቆመ ወይም ከቆመበት ቦታ ያንቀሳቀሰ፤

22. ለአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ ቅድሚያ ያልሰጠ፤

23. ወደ የማይሄድበት አቅጣጫ ምልክት ያሳየ፤

24. ከሚጠበው በላይ ጭስ እያጨሰ ወይም ዘይት ወይም ነዳጅ እያፈሰሰ የሚሄድ ተሽከርካሪን ያሽከረከረ፤

25. ከሰባት ዓመት በታች የሆነ ህጻንን ለደህንነቱ ሲባል በተሰራው ማቀፈያ ውስጥ ሳያስቀምጥ ያሽከረከረ፤

26. የትራፊክ ተቆጣሪ ትዕዛዝ ያልፈጸመ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሰጠ ወይም እንዲቆም ሲታዘዝ በእንቢተኝነት ሳይቆም የሄደ፤

27. በተራፊ ጭነት ላይ ተገቢውን ምልክት ሳያደርግ ወይም በተሽከርካሪው ላይ የተጫነውን ጭነት በሚገባ ሳያስር ወይም ሳይሸፍን ያሽከረከረ፤

28. በእግረኛ ማቋረጫ መንገድ ላይ ወይም ከእግረኛ ማቋረጫ በአስራ ሁለት (12) ሜትር ውስጥ ተሽከርካሪ ያቆመ፤

29. የእሳት አደጋ ተሽከርካሪ ውሃ መሙያ ቦታ ላይ ወይም በእሳት አደጋ መከላከያና በሆስፒታል መግቢያና መውጪያ በር ላይ ተሽከርካሪ ያቆመ፤

30. ባልተፈቀደ ቦታ ወይም ባልተወሰነ ሰዓት ወይም የለማጅ ምልክት ሳይለጥፍ አሽከርካሪ ማሽከርከር ያስተማረ ወይም ያለማመደ፤

31. የተሽከርካሪው በር ተከፍቶ እያለ ወይም ጨርሶ ሳይዘጋ ያሽከረከረ፤

32. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሮት የሚያሽከረክረውን ተሽከርካሪ ፈቃድ ለሌላው ወይም በዚህ ደንብ መሰረት ለታገደበት ሰው አሳልፎ የሰጠ፤

33. ተሽከርካሪው በአንቅስቃሴ ላይ እያለ ተሳፋሪ የጫነ ወይም ያወረደ፤

34. ባለ ሦስት ጎን አንጸባራቂ ምልክት በበቂ ርቀት ሳያስቀምጥ የተበላሸ ተሽከርካሪ ያቆመ፤

35. ከተፈቀደለት ጊዜ በላይ በማዘግየት ተሽከርካሪን በመንገድ ላይ ያቆመ፤

36. ተሽከርካሪውን ያለአግባብ ወደ ኋላ ያሽከረከረ፤

37. የእደጋ ጊዜ አገልግሎት ተሽከርካሪ በ100 ሜትር ርቀት ተከትሎ ያሽከረከረ፤

38. በተሽከርካሪ ማቆሚያ ሰፍራ ወይም በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ የጠገነ፤

ሐ/ ሶስተኛ ደረጃ የጥፋት ዝርዝር

1. የጉዞ ረድፉን ወይም መስመሩን ሳይጠብቅ ያሽከረከረ፤
2. የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ሞተር እየሰራና በተሽከርካሪው ውስጥ መንገደኞች እያሉ ነዳጅ መሙላት፤
3. ከተሽከርካሪው የመጫን አቅም በላይ ትርፍ ሰው የጫነ ፤
4. በምድቡ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሮት ከተፈቀደለት ደረጃ በላይ የሆነ ተሽከርካሪን ያሽከረከረ፤
5. ተንቀሳቃሽ ስልክ በእጁ ይዞ እያነጋገረ ወይም መልእክት እየጻፈ እየላከ ወይም እያነበበ ያሽከረከረ፤
6. የጭንቅላት መከላከያ (ሄልሜት) ሳያደርግ ወይም አድርጎ ሳያስር ወይም አብሮት የጫነው ሰው ማድረጉንና ማሰሩን ሳይረጋግጥ ሞተር ሳይክል ያሽከረከረ፤
7. በጭነት ተሽከርካሪ በሕግ ከተፈቀደለት ውጪ ሰውን ያሳፈረ፤
8. በማብሪያ ጊዜ መብራት ሣይኖረው ያሽከረከረ፤
9. ቴሌቪዥን ወይም ሌሎች ምስሎችን ተሽከርካሪ ውስጥ እየተመለከተ ያሽከረከረ፤
10. የደህንነት ቀበቶ ሳይስር ወይም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ ማሰራቸውን ሳያረጋግጥ ያሽከረከረ፤
11. ቀይ የትራፊክ መብራት የጣሰ፤
12. በተከለከለ መንገድ ወይም አቅጣጫ ያሽከረከረ፤

13. የትራፊክ ክብ ደሴትን በግራ ያቋረጠ፤

14. በድልድይ ላይ ተሽከርካሪ ያቆመ፤

15. ጫት ቅሞ ወይም እየቃመ ወይም አደንዛዥ ዕፅ ወስዶ ያሽከረከረ፤

16. በመስቀለኛ መንገድ ላይ ቅድሚያ ሊሰጠው ለሚገባ ተሽከርካሪ ቅድሚያ ያልሰጠ፤

17. በሕግ ከተፈቀደው ከፍታ፣ ርዝመት፣ እና ስፋት ውጭ ጭነት የጫነ፤

18. የመለያ ሠሌዳ ቁጥሩ ሊታይ የማይችል ቦታ ላይ ያሰረ ወይም የተደመሰሰ ወይም የተቆረጠ ወይም የተሸፈነ ወይም የተለያዩ ቀለማትን የቀባ ተሽከርካሪን ያሽከረከረ፤

19. ተሽከርካሪው የፊት ወይም የኋላ ሠሌዳ ሳይኖረው ያሽከረከረ፤

20. ተላላፊ ሠሌዳ ከተፈቀደለት ጊዜና ቦታ ውጪ የተጠቀመ፤

21. ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ጭነትን ከሕዝብ ጋር የጫነ፤

22. ለአውቶብስ ብቻ ተብሎ የተለየ መንገድ ላይ ያሽከረከረ ፤

23. በተሽከርካሪው የውጭ አካል ላይ ሰው የጫነ ፤

24. ከተሽከርካሪው የመጫን አቅም በላይ ትርፍ ሰው የጫነ 1500 ብር እና በጫነው በእያንዳንዱ ትርፍ ለተጫነ ሰው ተጨማሪ 100 ብር ይቀጣል፤

25. በጭነት ተሽከርካሪ በተፈቀደው አግባብ ካልሆነ በስተቀር በተሽከርካሪው የውጭ አካል ሰውን ያሳፈረ 1500 ብር እና በጫነው በእያንዳንዱ ትርፍ ለተጫነ ሰው ተጨማሪ 100 ብር ይቀጣል፤

CamScanner

2. ለጥፋቶቹ የሚቆጠር የቅጣት ነጥብ እና የቅጣት መጠን ወይም የሚወሰድ እርምጃ

ሀ/ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት ሲፈጸም

የጥፋቱ ደረጃ	ለጥፋቱ የሚመዘገብ ነጥብ	ለጥፋቱ የሚጣል የገንዘብ ቅጣት
1ኛ ደረጃ ጥፋት	1	500.00ብር
2ኛ ደረጃ ጥፋት	2	1000.00ብር
3ኛ ደረጃ ጥፋት	3	1500.00ብር
ልዩ ደረጃ ጥፋት	8-21	ለተለያዩ ደረጃ ያላቸው አጓዳዎች እና የገንዘብ ቅጣቶች
ሌሎች ደንብ መተላለፍ ጥፋቶች	0	ከ100-20000
በአግረኞች ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች	0	100-150
በትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች	0	

ለ/ ለሁለተኛ ጊዜ እና ከዚያ በላይ ጥፋት ሲፈጸም

ተቁ	ለጥፋቱ የሚመዘገብ ነጥብ	ለጥፋቱ የሚከፈል የገንዘብ መጠን
1	2-4	600
2	5-7	850
3	8-10	1600
4	11-13	2000
5	14-16	ለ6 (ስድስት) ወር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ታግዶ በአገልግሎቱ ወይም በሚመለከተው ሀጋዊ አካል የሚሰጠውን የዕውቀትና ከሀሎት ስልጠና ወስዶ እና የማሽከርከር ብቃቱ ተረጋግጦ ፈቃዱን መልሶ ማግኘት ይችላል፡
6	17-20	የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ለአንድ አመት ታግዶ ከቆየ በኋላ በአገልግሎቱ ወይም በሚመለከተው ሀጋዊ አካል የሚሰጠውን የዕውቀትና ከሀሎት ስልጠና ወስዶ እና የማሽከርከር ብቃቱ ተረጋግጦ ፈቃዱን መልሶ ማግኘት ይችላል፡፡
7	21 እና በላይ	አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለአንድ አመት ከስድስት ወር ታግዶ ከቆየ በኋላ በአገልግሎቱ የሚሰጠውን የዕውቀትና ከሀሎት ስልጠና እና የማሽከርከር ብቃቱ ተረጋግጦ ፈቃዱን መልሶ ማግኘት ይችላል፡፡

ሐ/ ቅጣትን በወቅቱ አለመፈጸም

ማንኛውም አሸከርካሪ በዚህ ደንብ መሰረት የተጣለበትን የገንዘብ ቅጣት ሳይከፍል ለሚዘገይባቸው ጊዜያት ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ በተመለከተው መሰረት ተጨማሪ የገንዘብ ቅጣትና የነጥብ ቅጣት ይጣልበታል።

ተቁ	ቅጣቱ የሚፈፀምበት ጊዜና የሚጣል ተጨማሪየገንዘብ ቅጣት መጠን	ተጨማሪ የነጥብ ቅጣት መጠን
ነ	እስከ ነዐኛው ቀን ድረስ ቅጣቱን የሚፈፅም የተጣለበትን የቅጣት መጠን ብቻ ይከፍላል	0
2	ነነ ቀን በኋላ ቅጣቱ የሚፈፅም ሰው ከአስራአንደኛው ቀን ጀምሮ ላሉት እያንዳንዱ ቀናት የቅጣቱን መጠን 5 በመቶ ወለድ እየተጨመረ ይቀጣል	ነ

SAMUEL GIRMA

CamScanner

መ/ ልዩ ደረጃ ጥፋት

ተቁ	የጥፋት አይነቶች	ቅጣት	ለጥፋቱ የሚመዘገብ ነጥብ
ሀ	ተሸከርካሪ በማሽከርካር በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም አሽከርካሪ	ሀ,600 ብር	8
2	በተሸከርካሪው ማናቸውንም አይነት ጥፋት በመፈፀም በሰው አካል ላይ ቀላል የአካል ጉዳት ያደረሰ አሽከርካሪ	ለስድስት ወር ይታገዳል	14
3	በተሸከርካሪው ማናቸውንም አይነት ጥፋት በመፈፀም በሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰ	ለአንድ አመት እገዳ	17
4	በተሸከርካሪው ማናቸውንም አይነት ጥፋት በመፈፀም በሰው ላይ ሞት ያደረሰ	ለአንድ አመት እገዳ	17
5	ግልፅ የሆነ ደንብ ወይም መመሪያ በሙተላለፍ ሁለት እና ከዛ በላይ የሞት ጉዳት ያደረሰ	ለአንድ አመት ከስድስት ወር እገዳ	21
6	የአልኮል መጠን በትንፋሽ ውስጥ 0.24-0.6 ሚሊ ግራም/ሊትር	ሀ,500 ብር	3
7	የአልኮል መጠን በትንፋሽ ውስጥ 0.6ሀ-0.8 ሚሊ ግራም/ሊትር	2,000 ብር	3
8	የአልኮል መጠን በትንፋሽ ውስጥ ከ0.8ሀ-ሀ.0 ሚሊ ግራም/ሊትር	2,000 ብር	8

9	የአልኮል መጠን በትንፋሽ ውስጥ 1.0 ሚሊ ግራም/ሊትር በላይ	3,000 ብር	8
10	ወጣት አሽከርካሪዎች፣ ጀማሪ አሽከርካሪዎች፣ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች፣ የንግድ ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች እና አደገኛ ጭነት የጫኑ ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች የአልኮል መጠን በትንፋሽ በየትኛውም መጠን ከተገኘ	2,000 ብር	8
11	ከተፈቀደ ፍጥነት በላይ እስከ አምስት ኪ/ሜ በሰአት	0	0
12	ከተፈቀደ ፍጥነት በላይ ከ6-10ኪ/ሜ በሰአት ሲበልጥ	1,500 ብር	3
13	ከተፈቀደ ፍጥነት በላይ ከ11-20ኪ/ሜ በሰአት ሲበልጥ	1,700 ብር	3
14	ከተፈቀደ ፍጥነት በላይ ከ21-30ኪ/ሜ በሰአት ሲበልጥ	1,800 ብር	3
15	ከተፈቀደ ፍጥነት በላይ ከ31-40ኪ/ሜ በሰአት ሲበልጥ	2,000 ብር	8
16	ከተፈቀደ ፍጥነት በላይ ከ41ኪ/ሜ በሰአት ሲበልጥ	2,500 ብር	8
17	ከተፈቀደ ፍጥነት በላይ ከ50ኪ/ሜ እና ከዛ በላይ በሰአት ሲበልጥ	3,500 ብር	8

CamScanner

18	የትራፊክ ግጭት ወይም ጉዳት አድርሶ በቦታው ላይ ያልቆመ፣ ወይም ባደረሰው የትራፊክ ጉዳት የተጎዳውን እና ሕክምና የሚያስፈልገውን ሰው ወደ ህክምና በመውሰድ እንዲታከም ያላደረገ	በወንጀል ህጉ መሰረት ይጠየቃል	21
19	የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ታግዶበት ሳለ ያሽከረከረ	3,000 ብር	8
20	አፈር፣ አሸዋ፣ ድንጋይና ተመሳሳይ ነገሮችን የሚመለከተውን አካል ሳያስፈቅድ በተሸከርካሪ ወይም በአግረኛ መንገድ ላይ ያራገፈ. አሽከርካሪ	3,000 ብር	8
21	ያበላሸውን መንገድ መጠገኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሰንሰለት የሚሸከረከር ልዩ ተንቀሳቃሽ በመንገድ ላይ ያሽከረከረ	7,000 ብር	8
22	ፍጥነት የሚያዛባ ቴክኖሎጅ በመጠቀም ከተፈቀደ ፍጥነት በላይ በሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ያደናቀፈ.	10,000 ብር የገንዘብ ቅጣት እና ተሸከርካሪው ላይ የተገጠመውን ህገወጥ አደናቃፊ መሳሪያ መውረስ	11
23	አፈር፣ አሸዋ፣ ድንጋይና ተመሳሳይ ነገሮችን የሚመለከተውን አካል ሳያስፈቅድ በተሸከርካሪ ወይም በአግረኛ መንገድ ላይ ያራገፈ. አሽከርካሪ	3,000 ብር	8

CamScanner

ሠ/ ሌሎች የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

ተ.ቁ	የጥፋቶች ዝርዝር	የገንዘብ ቅጣት መጠን
1	በማብሪያ ጊዜ በጉልህ የሚታይ መብራት ሳይገዛና ለተሸከርካሪው አቅራቢያ በሆነው ጎን መብራቱን ሳያሳይ እንስሳትን የነዳ ማንኛውም የእንስሳት ጠባቂ	100 ብር
2	ከማዘጋጃ ቤት ሰራተኞች ወይም ከተፈቀደላቸው ሰዎች በስተቀር በተሸከርካሪ መንገድ ላይ በእጅ የሚገፋ ባለመንኩራኩር ወንበርን ወይም የሚሰብ ጋሪን የገፋ ወይም የሳበ ማንኛውም ሰው	100 ብር
3	ለመጫወቻ እና ለጊዜ ማሳለፊያ ተብሎ የተሰራ ብስክሌት ወይም በጫማ መልክ የሚጠለቅ ተንሸራታች ወይም ሌሎች መጫወቻዎችን በተሸከርካሪ መንገድ ላይ ወይም የተጠቀመ ማናቸውም ሰው	100 ብር
4	በብስክሌት ላይ የተዘጋጀው መቀመጫ ላይ ተመቻችቶ ሳይቀመጥ ወይም የብስክሌቱ መሪ በሁለት እጁ ሳይዝ እና በእግሮቹም መርገጫውን ሳይረግጥ ብስክሌት የነዳ ማንኛውም ሰው	100 ብር
5	ብስክሌት በሚያሽከረክርበት ጊዜ በማናቸውም እኳኋን በመጓዝ ላይ ያለ ሌላን ተሸከርካሪ ወይም ሌላን ብስክሌት ይዞ የነዳ ማንኛውም ሰው	100 ብር
6	በመንገድ ላይ እንስሳትን የነዳ ወይም ይዞ የተገኘ ማንኛውም ሰው	200 ብር
7	በተሸከርካሪ ላይ ተገቢ ያልሆነ አካል የጨመረ ወይም ከተፈቀደለት ወንበር ውጭ ተጨማሪ ወንበር ወይም መቀመጫ የጨመረ የተሸከርካሪ ባለንብረት	400 ብር

SAMUEL GIRMA

CamScanner

8	በሀዘን ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ከሚመለከተው አካል ፍቃድ ሳይኖረው የተሸከርካሪዎችን ወይም የእግረኞችን እንቅስቃሴ የሚያውክ ቁሳቁስ ወይም ሽቀጥ በእግረኛ ወይም በተሸከርካሪ መንገድ ላይ ያስቀመጠ፣ የተከለ፣ የንግድ ስራ የሰራ ወይም ተመሳሳይ ነገሮች ያከናወነ ማንኛውም ሰው	5,000 ብር
9	በማብሪያ ጊዜ በጉልህ የሚታይ መብራት ሳይዝ እና ለተሸከርካሪው አቅራቢያ በሆነው ጎን መብራቱን ሳያሳይ እንስሳት የነዳ ማንኛውም የእንስሳት ነጋዴ	500 ብር
10	ማንኛውም የመንገድ ምልክት ያነሳ ወይም ያበላሸ ወይም ከቆመበት ያዛወረ ወይም የለወጠ ወይም በማንኛውም አኳኋን እንዳይታይ ወይም እንዳይታወቅ ያደረገ ማንኛውም ሰው	1,000 ብር
11	ያበላሸውን መንገድ መጠገኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ያለፈቃድ ተሸከርካሪ ወይም እግረኛ መሄጃ መንገድን የቆፈረ፣ ያበላሸ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ያከናወነ ማንኛውም ሰው	3,000 ብር
12	ከባለቤትነት ወይም በይዞታው የተያዘውን ተሸከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለሌላው ሰው አሳልፎ የሰጠ ማንኛውም የተሸከርካሪ ባለንብረት	3,000 ብር
13	የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው ተሸከርካሪ ያሽከረከረ ማንኛውም ሰው	5,000 ብር
14	የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው ተሸከርካሪ በማሽከርካር በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው	7,000 ብር
15	ከፖሊስ በተሸከርካሪው ላይ የደረሰውን የጉዳት አይነት የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ ሳይቀበሉ ጥገናውን ያከናወነ ጋራዥ/የጋራዥ ባለቤት/	በወንጀል ህጉ የሚያስጠይቀው እንደተጠበቀ ሆኖ 20,000 (ሀያ ሽህ) ብር ይቀጣል
16	አመታዊ የተሸከርካሪ ምርመራ ያላደረገ የተሸከርካሪ ባለንብረት	3,000 ብር

ረ/ እግረኞች ስለሚቀጡበት

ተ.ቁ	የጥፋቶች ዝርዝር	የገንዘብ ቅጣት መጠን
1	ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርግ መንገድ ያቋረጠ	100 ብር
2	ለተሸከርካሪ የተፈቀደ መንገድ ላይ ያለበቂ ምክንያት የቆመ ወይም የተጓዘ	100 ብር
3	እግረኛ መንገድ በሌለበት መንገድ ቀኝ ጠርዙን ይዞ የተጓዘ	100 ብር
4	ለእግረኛ መንገድ ተብሎ ከተከለለ መንገድ ውጭ የተጓዘ	100 ብር
5	በብረትም ሆነ በግንብ ተለይተው የታጠሩ መንገዶች ዘሎ መንገድ ያቋረጠ	150 ብር
6	በጆሮ ማዳመጫ የተለያዩ ድምፆችን እያዳመጠ መንገድ ያቋረጠ	150 ብር
7	ለእግረኛ ከልከል ነው የሚል ምልክት ባለበት መንገድ ወይም እግረኛ እንዳያቋርጥ በተከለከለበት የማሳለጫ ወይም የቀለበት መንገድ ያቋረጠ	150 ብር
8	በዚህ ሰንጠረዥ ከተራ ቁጥር 1 እስከ ሰባት ካሉት ጥፋቶች አንዱን ፈፅሞ ከፍያ መፈፀም ያልቻለ ወይም ያልፈለገ ማንኛውም ሰው	ተመጣጣኝ የሆነ ማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

ሰ/ በትራፊክ ተቆጣጣሪዎች የሚፈፀሙ ጥፋቶች እና የሚያስከትሉት ቅጣት

ተ.ቁ	የጥፋት አይነት	የሚወሰድ እርምጃ
1	የትራፊክ ቁጥጥር ተግባሩን ሲያከናውን ለመንገድ ተጠቃሚዎችና ለደንብ ተላላፊዎች ሙያው የሚጠይቀውን ተገቢውን አክብሮት ያላሳየ፣ ያመናጨቀ ወይም የተሳደበ በማንኛውም ምክንያት አድሎ የፈፀመ በዚህ ደንብ ከተደነገገው ውጭ በተለይም ጥፋተኛ ባልሆነ የመንገድ ተጠቃሚ ላይ አላግባብ የደንብ መተላለፍ ቅጣት የወሰነ እንደሆነ	አግባብነት ባለው ህግ በዲሲፕሊን የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።
2	ጉቦ የተቀበለ ወይም የጠየቀ እንደሆነ ወይም በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከላይ በተራ ቁጥር አንድ ከተገለፀት ጥፋቶች አንዱን በድጋሚ የፈፀመ እንደሆነ	አግባብነት ባለው ህግ በወንጀል እና በዲሲፕሊን የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከትራፊክ ተቆጣጣሪነት ሀላፊነቱ እንዲነሳ ይደረጋል።

SAMUEL GIRMA

CamScanner